
# ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ገብረማርያም

/፲፰፻፹፰ – ፲፱፻፹፩/

በተስፋዬ ሽብሩ



በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር መዓርግ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበሩ

⇒ በ፲፱፻፳ ዓ.ም ወደ ምድረ ግብፅ ተጉዘው መዓርገ ክህነት ተቀበሉ፤

⇒ በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም የራስ ኪዳነ ማርያም ጉብረ መስቀል ጸሐፊ ሆኑ፤

⇒ በ፲፱፻፴ ዓም መልአከ ሰላም ተብለው የሠራዬ አውራጃ ሊቀ ካህናት ሆኑ፣

⇒ በ፲፱፻፵፬ ዓ.ም የአገር ፍቅር ማኅበርን መሠረቱ፣

⇒ በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም ማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖትን አቋቋሙ፣

⇒ በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም የሠራዬ አውራጃ የአገር ፍቅር ማኅበር ፕሬዚዳንት ሆነው ተመረጡ፣

⇒ በ፲፱፻፵፪ ዓ.ም ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤትን መሠረቱ፣
⇒ በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም የኤርትራ ምክር ቤት አባል ሆነው ተመረጡ፣
⇒ በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የኤርትራ ምክር ቤት ም/ፕሬዘዳንት ሆነው ተሾሙ፤
⇒ በ፲፱፻፶፭ ዓ.ም የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ም/ፕሬዚዳንት ሆነው ተሾሙ፣
⇒ በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም ንቡረ እድ ተብለው የአክሱም ጽዮንና አውራጃዎዋ አስተዳዳሪነት ተሾሙ፣
⇒ ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ጡረታ እስከ ወጡበት ፲፱፻፷፪ ዓ.ም ድረስ በሚኒስትር ማዕርግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅ ላይ ቤተ ክህነት የቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በመሆን አገል ግለዋል።

«ከ፲፱፻፶፪ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፷፪ ዓ.ም ድረስ የኤርትራ የፕሬስ ኃላፊና ጋዜጠኛም ሆኜ በቆየሁባቸው ዓመታት በቅርበት ካወቅኋቸው ታላላቅ ሰዎች አንዱ ክቡር ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም ናቸው። ገጸ አረጋዊነታቸው አለባበሳቸውና አነጋገራቸው ለየት ያለ ግርማ ሞገሳዊነትን አልብሷቸዋል። በቀረብኳቸው ቁጥር እየወደድኳቸውና ከልቤ እያከበርኳቸው ሄድኩ።»

ክቡር ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም ታሪካቸው ሊዘከር ላቸው ከሚገባቸው ጥቂት ኢትዮጵያውያን አንዱ ናቸው። ባላቸው የሀገር ፍቅር ስሜት የኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ኤርትራን ከኢትዮጵያ ነጥሎ ይገዛ በነበረበት ዘመን ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ እንድትቀላቀል የአባቶቻቸውን ሕይወታቸውን እንኳን መሥዋዕት ለማድረግ የደፈሩ የአቡነ ጴጥሮስንና የአቡነ ሚካኤልን መንገድ ለመከተል ያላንገራገሩ የሀገርም የቤተ ክርስቲያንም መኩሪያ ነበሩ።

መንፈሳዊነታቸው፣ ለሰዎች ኑሮ መበልጸግ ማሰባቸው፣ ለሕዝቦች አንድነትና ሰላማዊነት መታገላቸው፣ ለዕውቀትና ልማት ዘወትር የሚጥሩ መሆናቸው ሁልጊዜ ይታወሰኛል። አሥመራም ሆነ አዲስ አበባ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ እጠይቃቸው ስለነበር እጅግ ብዙ ብዙ ጉዳዮችን አጫውተውኛል።





ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሚያዝያ ወር ፲፱፻፹፫ ዓ.ም ከስደት እንደ ተመለሱ ክቡር ንቡረ እድ ድሜጥሮስ በሐምሌ ወር ፲፱፻፹፫ ዓ.ም በምሥጢር ከኤርትራ አዲስ አበባ መጥተው ከግርማዊነታቸው ዘንድ ቀርበው "ኤርትራ አገርዎ ናት፤ ከቅኝ ገዥዎች ቀንበር ፈልቅቀው ወደ እናት አገርዋ እንዲቀላቅሏት አደራ" ባሏቸው ጊዜ "እኛም ይህንኑ ስለምናምንበት ነው፤ ገና ካርቱም እያለን በዐዋጃችን ያስታወቅነው" ስላሉኝ ነው ጥረቱን የጀመርነው ብለውኛል።

በኤርትራ ጀምረውት የነበረው የመንፈሳዊ ትምህርትና ጥበበ እድ በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ብርቱ ጥረት አድርገዋል። ሁሉንም አሟልቶ የሰጣቸው የሀገርና የሃይማኖት ተቆርቋሪ፣ የአስተዳደር መሪ ነበሩ።» በማለት የንቡረ ዕድ ድሜጥሮስን ማንነት የተናገሩት ታዋቂው ጋዜጠኛና ደራሲ አቶ እኝህን የሀገር ባለውለታ በማወቄ ክብር ይሰማኛል።» በማለት የንቡማሞ ውድነህ ናቸው።

በዚህ ዙሪያ ስለ ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ብዙ ሊባል የሚችል ነገር ቢኖርም ለዚህ ጽሑፍ አስፈላጊ የሚሆነውን ሐሳብ ብቻ ለማንሣት ተሞክሯል። በዚህ ረገድ ሌሎች ብዙ ሊሉበት ይችላሉ የሚል እምነት አለን።

## ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም

ከመምህር ገብረ ማርያም ፍሥሐና ከወ/ሮ ወለተ አብ ማዕቀብ መስከረም ፲፪ ቀን ፲፰፻፹፰ ዓ.ም በቀድሞው የኤርትራ ክፍለ ሀገር በሠራዬ አውራጃ በዓረዛ ወረዳ ምድሪ ወዲ ሰበራ ማይጩው ማይድማ ከተባለው ሥፍራ ተወለዱ። ወላጆቻቸው ያወጡላቸው ስም ኪነ ሥላሴ (የሥላሴ ጥበብ) የሚል ነበር። ዕድሜያቸው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ ከወላጅ አባታቸው ፊደል ቆጥረው ዳዊት በመድገም መዓርገ ዲቁና ተቀበሉ። በመቀጠል ከመምህር ገ/ሚካኤል ዜማ፣ ጾመ ድጓና ምዕራፍ በመማር የዕውቀት አድማሳቸውን ማስፋት ቻሉ። ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ለትምህርት በነበራቸው ጥልቅ ፍቅር የተነሣ የትውልድ መንደራቸውን ጥለው ለመሄድ ተገደዱ። ወደ ጎንደር ክፍለ ሃገር በመሄድ በደብረ ሚካኤል ወንበር ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት ከጌቴ ገሞራው ዘንድ ቅኔን ከነአገባቡ ተማሩ። ከዚያም ወደ ጭልጋ አውራጃ

በመሄድ ከመምህር መርሻ ለሁለተኛ ጊዜ ቅኔን አስፋፍተዋል። በመ-
ቀጠል ወደ ጎንደር ከተማ ተመልሰው አደባባይ ኢየሱስ አቋቋምን ያስተምሩ ከነበሩት ከመምህር መኰንን ዘንድ አቋቋምን ተማሩ። ወደ ደብረ ዓባይ ተሻግረውም መዝገበ ቅዳሴን ተምረው አስመስክረዋል።

የወጣትነት ጊዜያቸውን ትምህርት በመቅሰም ያሳለፉት ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ወደ ትውልድ ሀገራቸው በመመለስ አገልግሎት ጀመሩ። አስተዋይነታቸውና ብልህነታቸው በሁሉም ዘንድ ይታወቅ ስለነበር ራስ ኪዳነ ማርያምም ይህንኑ ተረድተው ጸሐፊያቸው አድርገዋቸው ነበር። እርሳቸው በሌሉበትም እንዲያስተዳድሩ ወክለው ሲልኳቸው የተናገር ከው ቀለም /የተናገርከው የሚደመጥ/፣ የረገጥከው ለምለም ይሁንልህ፣ እሾህ አይውጋህ፣ አጥር አያግድህ እያሉ ይመርቋቸው ነበር። ንቡ ረ እድም የተላኩበትን ሥራ አጠናቀውና አስፈጽመው ይመጡ እንደ ነበር ይነገርላቸዋል። አቡነ ማቴዎስ በ፲፱፻፲፱ ዓ.ም ከሞቱ በኋላ በኢ ትዮጵያ ጳጳስ አልነበረም። ቢኖርም ኤርትራ በጊዜው በኢጣሊያ ሥር ስለነበረች መንፈሳዊ ግንኙነትም ከመሐል ሀገር ጋር እንዳይኖር ይከለ-
ከል ነበር። በዚህ የተነሣ በ፲፱፻፳፫ ዓ.ም ከብዙ ሰዎች ጋር በመሆን
ምድረ ግብፅ ተጉዘው ከሊቀ ጳጳሳት አባ ዮሐንስ እጅ መዓርገ ቅስ ናንና ድሜጥሮስ የሚለውን ስያሜ ተቀብለው ተመለሱ። /በቤተ ክርስ ቲያን ሥርዓት ርእሰ አድባራት የሚል መጠሪያ ላላቸው አብያተ ክርስ ቲያ፡፡ አለቆች የሚሰጥ ሹመት ነው።/

በወቅቱ የግብፅ (የምስር) እና የኢትዮጵያን የጥንት ወዳጅነትን አስመልክተው ወደፊትም በፍቅርና በአንድነት እንዲቀጥሉ "ዮም አሐደ መርዔተ ኮነ መላእክት ወሰብእ ከመ ይሰብሕዎ ለክርስቶስ በቃለ አሚን" በልደት መላእክትና እረኞች አንድ ሆነው ለእግዚአብሔር ምስጋና እንዳቀረቡ እኛም መንፈሳዊ አንድነት እና አፍሪካዊ ወንድማማ ችነታችን ማደ ለማደ ቢሆንም በዚህ ዕለት ከፓትርያርኩ እና ከሊቃነ ጳጳሳቱ እንዲሁም ከግብፅ ሕዝብ ጋር አንድ እንድንሆን ያደረገ እግዚ አብሔር ይመስገን በማለት የተናገሩት ንግግር በዚያ የተገኙትን ሁሉ ያስደመመ ነበር።





ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ክህነት ከተቀበሉ በኋላ ግብፃውያን ጳጳሳትና መኳንንት በተሰበሰቡበት ስለ ኢትዮጵያና ግብፅ ግንኙነት ተናግረው ሰማዕያኑን እንዳስደሰቷቸው ይነገራል። ወደ ሠራዬ ከተመለሱ በኋላ የአውራጃው ሊቀ ካህናት ተብለው ለ፲፭ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንን አገ ልግለዋል። በ፲፱፻፴፪ ዓ.ም የኤርትራው ጳጳስ አቡነ ማርቆስ መልአከ ምሕረት ብለው ሾመዋቸዋል። በኋላም መልአከ ሰላም ተብለዋል።

በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም የኢትዮጵያ ነፃነት ከተመለሰ በኋላ ኤርትራም ነፃነ ቷን አግኝታ ከእናት ሀገሯ እንድትቀላቀል ጽኑ ፍላጎት ስለነበረ ሀገር ፍቅር የሚባል ማኅበር በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም ተመሠረተ። ንቡረ እድ ድሜጥሮስም ከመሥራቾች አንዱ በመሆን ሕዝቡን ለነፃነት ያነሳሱ፣ ስለ ሐቀኛ የኢትዮጵያዊነት ታሪክ ያስተምሩ የነበሩ ሀገር ወዳድ ናቸው። የደቂ ወረዳ ወኪል ሆነው ቅስቀሳ በሚያካሂዱበት ጊዜ በእንግሊዞች እጅ ወድቀው አንድ ዓመት ታስረዋል። በነበራቸው የሀገር ፍቅር ስሜት የተነሣ በቆራጥነት በመቆማቸው በማይደግፉ ኃይሎች ሁለት ጊዜ ቦምብ ተወርውሮባቸው ከአንደኛው ሲያመልጡ በአንዱ ቆስለዋል። በዚሁ የተነሣ ሆስፒታል ተኝተው በነበረበት ጊዜ ግርማዊ ንጉሠ ነገ ሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሊጠይቋቸው ሄደው "የፈሰሰው ደምዎ የኢት ዮጵያን አንድነት ያጠነክራል" በማለት አጽናንተዋቸዋል።

ጣልያናውያን የኤርትራን ሕዝብ ከኢትዮጵያዊ ባህሉና ሃይማኖቱ በመለያየትና የራሳቸውን ፍላጎት በመጫን እንቅስቃሴያቸውን አጠናክ ረው እንደ ነበር ይታወቃል። ሚስዮናውያኑ በዚህ ሁኔታ ሲንቀሳቀሱ በገበያ የሚታየው መጽሐፍ በአብዛኛው የካቶሊክና የፕሮቴስታንት ብቻ ነበር። ንቡረ እድም ይህንን በመረዳት በእኛ ስንፍና ሚሲዮናውያኑ ወጣቶቻችንን ከጉያችን እየነጠቁ ይወስዱብናል። ሃይማኖታችንም ይበ ረዛል በማለት ተነሣሥተው በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት የተባለ ማኅበር አቋቋሙ። ይህ ማኅበር ወንጌልን በማስፋ ፋትም ሆነ ሕዝበ ክርስቲያኑን በትምህርት በማነፅ ከፍ ያለ አገልግሎት ፈጽሟል። ይህ ማኅበር በወቅቱ የባህል ወረራውንና የሃይማኖት ቅሰ ጣውን የሚከለክልበትና ምእመናንን የሚያስተምርበት «ዜና ሐዋር ያት» የተባለ በየወሩ እየታተመ የሚወጣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሃይማኖትን እምነትና ሥርዓት ጠብቆ የሚወጣ ጋዜጣ ነበር:: ማኅበሩ
«ኮከበ ጽባሕ» በሚል ማተሚያ ቤት አቋቁሞ አርባ ስድስት  መጻ-
ሕፍተ ብሉያትን በግእዝና በአማርኛ፣ ሃያ ስድስት መጻሕፍተ ሐዲሳ
ትን በግእዝና በአማርኛ፣ መጽሐፈ ሰዓታትን ዳዊትና ሌሎችንም በር
ካታ መጻሕፍት እያሳተመ ለቤተ ክርስቲያናችን በማቅረብ ለምእመናን
እንዲሠራጭ አድርገዋል:: የመጻሕፍት ኅትመት ነገር ሲነሣ ንቡረ እድ
ድሜጥሮስ ያሳተሙት የብሉያትና የሐዲሳት መጻሕፍት  ከአማርኛ
ትርጓሜ ጋር መታተሙ ቀዳሚ ቦታ የሚሰጠው ይሆናል:: ብሉዩ
በሦስት ቅጽ ሐዲሱ በአንድ ቅጽ ተጠናቆ ቀርቧል:: "እንዲህ የመሰለው
ሥራ ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ አልነበረም" ሲሉ ዶ/ር ሥርግው ሐብለ
ሥላሴ የቤተ ክርስቲያን የአማርኛ መዝገበ ቃላት በተባለው መጽ-
ሐፋቸው ጠቅሰውት ይገኛል::

ንቡረ እድ በማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት ቅዱሳት መጻሕፍ
ትን በማሳተም ብቻ አልተገቱም:: በርካታ ትምህርት ቤቶችን በማሳነፅ
ለዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት የበኩላቸውን ድርሻ የተወጡ ታላቅ
አባት ነበሩ:: በአሥመራ ከተማ ደብረ ቤቴል አዳሪ ት/ቤት፣ ማኅደ
ረ ብርሃን፣ ቀራንዮ ት/ቤት፣ ማኅደረ ማርያም፣ መካነ ሕይወት ትምህ
ርት ቤት ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: ከዚሁ ጎን ለጎን መንፈሳዊ ትምህር
ቶችን በደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ጸዋትወ ዜማ፣
መዝገበ ቅዳሴ፣ ቅኔ፣ በደብረ ማዕዘን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን
መዝገበ ቅዳሴና ትርጓሜ መጻሕፍት እንዲሰጥ አድርገዋል:: በቀድሞዋ
የኤርትራ ክፍለ ሀገር የተለያዩ አውራጃዎችና በሌሎችም ቦታዎች ቤተ
ክርስቲያን ሲያሠሩ ዘመናዊ ት/ቤቶችም ለማቋቋም የበቁ የዘመኑ የሥ
ልጣኔ መሠረት የገባቸው የቤተ ክርስቲያን ዓምድ ነበሩ ለማለት
ያስችላል::

በአሥመራ ከተማ፣ በምጽዋ፣ በምዕራብ ኤርትራ ከዘጠኝ በላይ
የሆኑ አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነፅ የየአካባቢውን ምእመን ችግር
ለማቃለል የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል:: መካነ ሕይወት መድኃኔ
ዓለም፣ መርሶ አስሚር ቅዱስ ሚካኤል፣ ገሊላ ማርያምና ደብረ ኢየ
ሱስ ዋና ዋናዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው::





ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ረገድ ያበረከቱት አስተዋፅዖ በቀላሉ
የሚገመት አይደለም:: ኢ-አማንያንን በማስተማር አጥምቀው ወደ ክር
ስትና መልሰዋል:: እነሱንም ለመንከባከብና በእምነታቸው ለማጽናት
ቤተ ክርስቲያንና ትምህርት ቤት ከፍተውላቸዋል::

ቤተ ክርስቲያን ከመንፈሳዊ ተግባሯ በተጨማሪ በልማት ሥራዎች
መሳተፍና ራሷን መቻል እንዳለባት ከዘመናቸው ቀድመው የተረዱ
የቤተ ክርስቲያን ፈርጥ ነበሩ:: ለዚህ ደግሞ ማስረጃ መጥቀስ የሚያስ
ቸግር አይሆንም:: በ1961 ዓ.ም የቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽ/ቤት በሚኒስ
ቴር ደረጃ ሥራ አስኪያጅ ተብለው በተሾሙ ጊዜ የሠሯቸው ተግ
ባራት ምስክሮች ይሆናሉ:: በመንበረ ፓትርያርክ ግቢ ለ14ቱ አህጉ
ረ ስብከት ጳጳሳት ማረፊያ ቤቶች፣ በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ ኮ
ልፌ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ዳቦ መጋገሪያና የሻማ ፋብሪካ፣
አቋቁመዋል:: አነስተኛ ደመወዝ ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ለመ
ርዳት በማሰብ የማረሻ መኪና ከውጪ በማስመጣት እርሻ ማሳረስ ጀም
ረው እንደነበር የሚያውቋቸው ሰዎች ያስታወሳሉ:: በጉደርና በባኮ የወ
ይን ተክልን በማልማት ቤተ ክርስቲያን እንድት ጠቀም ሥራውን ወጥ
ነው እንደነበር የሚያውቋቸው ሰዎች ያስታውሳሉ:: ከዚሁም ጋር በተ
ያያዘ በመናገሻ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚውል የንጹሕ ስንዴ
እርሻ ልማት ዕቅድ ዘርግተዋል:: የቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ትምህ
ርት ቤትን አሳድሰዋል:: ለተማሪዎቹና ለአካባቢው ሕዝብ የሚያገ
ለግል የዳቦ መጋገሪያ አቋቁመዋል::

እስከ ፲፱፻፶፱ ዓ.ም ድረስ መልአከ ሰላም ተብለው ሲያገለግሉ
ቆይተው በዚሁ ዓመት የርእሰ አድባራት ወገዳማት የአክሱም ጽዮን
ቤተ ክርስቲያን ንቡረ እድ ተብለው በግርማዊ ጃንሆይ መልካም ፈቃድ
ይሾማሉ:: በዚህ ጊዜ በመጀመሪያ የወሰዱት እርምጃ የሕዝቡን ችግር
ግምት ውስጥ በማስገባት የአክሱም ነዋሪ ለብዙ ጊዜያት አብሮት የኖ
ረው የውኃ ችግር እንዲቃለል ማይሹም በተባለው የውኃ ማጠራቀሚያ
ላይ መጠኑን በማሳደግ አሠርተው ሕዝቡ ውኃ ሳይቸገር እንዲያገኝ
ማድረጋቸው በአካባቢው ሕዝብ ሲታወስ የሚኖር ተግባር ነው::

ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ አክሱም ጽዮንን ያስተዳድሩ በነበረ ጊዜ ለአካ
ባቢው ሕዝብ በርካታ ጠቃሚ ተግባራትን አከናውነዋል:: ቀደም ሲል

በአክሱም ጽዮን የኅዳር ጽዮንና የሆሳዕና በዓል ሲከበር ድል ያለ ድግስ ይደገሳል:: የአካባቢው ሕዝብም ይህንን ለማድረግ ሲል ከአቅሙ በላይ የሆነ ከፍተኛ ወጪ ያወጣል:: የድግሱንም መጠን "ኀምሳ ጋን ጠላ እንበለ አተላ፤ ኀምሳ ጋን ጠጅ እንበለ አንቡላ፤ ኀምሳ ፍሪዳ ቀርኑ ሰማይ ጠቀስ ጅራቱ ምድር አበስ (መሬት የሚጠረግ)":: በማለት ይገልጹት ነበር:: ንቡረ እድ ድሜጥሮስም እንዲህ ያለውን ሸክም ከድሃው ሕዝብ ላይ በማንሣት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንዲቆም አድርገዋል::

ንቡረ ዕድ ጌታ መከየ እግዚኡ በተባለ ቦታ የሕዝቡን የውኃ ችግር እጦት ተመልክተው በድማሚት ሰፊ ቦታ ማስቆፈር ጀምረው ገንዘብ አሰባስበው ለሥራ ሲንቀሳቀሱ በወቅቱ የትግራይ ገገር ከነበሩት ራስ መንገሻ ሥዩም ጋር በአንዳንድ የአፈጻጸም ሂደቶች ሳይስማሙ በመቅረታቸው ተቀይረው ወደ አዲስ አበባ ሊመጡ ችለዋል::

የአክሱም ሊቃውንት ሲታመሙ በግል ገንዘባቸው አሥመራ ድረስ በመውሰድ ያሳክማሉ፤ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ሊቃውንት ሊደረግላቸው የሚገባውንና ማግኘት የሚገባቸውን እንዲያገኙ፣ ጉባኤያቸውም እንዲሰፋ፣ ተተኪ ሊቃውንት እንዲያፈሩ የበኩላቸውን ጥረት አድርገዋል::

በሠሩበት ቦታ ሁሉ ባለጉዳይ በክርክርና በመመላለስ ጊዜውንና ጉልበቱን እንዳያባክን ጠዋት ወደ ቢሯቸው ከመግባታቸው በፊት ባለ ጉዳዮች መካከል ገብተው አቤቱታዎችንና ቅሬታዎችን በመስማት ለባለ ጉዳዮች የሚፈልጉት እንዲፈጸምላቸው ፍትሐዊ ውሳኔ ይሰጣሉ:: በዚህም ማንኛውም ባለጉዳይ የመጣበት ተፈጽሞለትና ሠምሮለት ይመለስ እንደነበር ዛሬም ድረስ ይነገራል::

በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም በሚኒስትር መዓርግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው በተሾሙበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ከቀድሞ ጀምሮ ትጠብቀው የነበረውን የራስዎን ፓትርያርክ መርጣ ለመሾም የቻለችበት ጊዜ ነበር:: ይህም ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጋር በመተባበር ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ የሰጡት ጥበብ የተሞላበት የአመራር ችሎታ ውጤት ነው ለማለት ይቻላል::





ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ኢትዮጵያ ሀገራቸውን ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውን እጅግ አድርገው የሚወዱ ታላቅ አባት መሆናቸውን ከተግባራቸው መረዳት ይቻላል:: ስለዚሁ ጉዳይ በአንድ ወቅት ሲናገሩ "ሁላችሁም እንደምታስታውሱት 'ኢትዮጵያ ወይም ሞት' ብለን ከተነሣንበት ከ፲፱፻፴፬ ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁኑ ሰዓት ስለ ኢትዮጵያ አገሬና ስለ ተዋሕዶ ሃይማኖቴ፤ የኢትዮጵያ አገሬ ጉሮሮ የሆኑት የምጽዋና አሰብ ወደቦች ከዐረቦች እጅ ላይ እንዳይወድቁ እጨነቅ ነበር:: ይህ ከነበረኝ የሀገር ፍቅር ተነሣሥቼ ከምጽዋ እስከ ተሰነይ፤ ከሐማሴን እስከ ዓዲግራት እየተንቀሳቀስኩ ሕዝቡን በመቀስቀስ አሯሯጥ በነበረ ጊዜ ጠላቶች በየጊዜው የኔን ሕይወት ከማጥፋት የተቆጠቡበት አንዳችም ቀንና ሰዓት የለም:: . . . ስለዚህ ለእውነተኛው ዓላማ ለኢትዮጵያ የምናፈሰው ደም የምንከፍለው የሕይወት መሥዋዕትነት የተቀደሰ ነው» ይሉ ነበር::

ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንደተቀላቀለች መጀመሪያ የኤርትራ ምክር ቤት አባል በመቀጠል የምክር ቤቱ ምክትል ፕሬዝዳንት ሆነው አገልግለዋል::

ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ የንግግር ተሰጥኦ የታደሉ ቀልጣፋና አንደበተ ርቱዕ ሲሆኑ ተናግረው የማሳመንና ሰዎችን ወደ ራሳቸው አቅርብ የማምጣት ልዩ ችሎታ ነበራቸው::

ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ከወ/ሮ ምዕራፍ ኣርዓዶም ጋር ጋብቻ ፈጽመው ሰባት ወንዶችንና ሁለት ሴት ልጆችን አፍርተዋል:: በ1966 ዓ.ም በጡረታ ተገልለው ማኅበረ ሐዋርያትን በመምራት ላይ እንዳሉ በተወለዱ በዘጠና አምስት ዓመታቸው መስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም አዲስ አበባ ዐርፈው ሥርዓተ ቀብራቸው መስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ራሳቸው ባሳነፁት በአሥመራው ደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል::

ወ/ሮ ግደይ ድሜጥሮስ የንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ሁለተኛ ልጅ ሲሆኑ ስለአባታቸው ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡን ጠይቀናቸው:- የሚከተለውን አጫውተውናል::

አባታችን ብዙውን ጊዜውን የሚያሳልፈው በሥራ ነው:: ሃገሩንም በጣም ይወዳል:: ለሃይማኖቱ ያለው ፍቅርና ጽናት ዛሬም ድረስ

ሳስታውሰው ያስደንቀኛል:: ሁላችንም ልክ እንደሱ እንድንሆን ይፈ-
ልጋል:: የዘወትር ንግግሩ በሃይማኖታችሁ ጠንካራ ሁኑ ሀገራችሁን
ውደዱ የሚል ነበር:: እኛም የሱን ያህል ባይሆንም አቅማችን የፈቀ
ደውን ያህል የሚለንን ለመፈጸም እንሞክራለን:: እርሱ በፍጹም የዓ
ለም ነገር አያምረውም ስለ ኑሮውም ብዙም የሚጨነቅ አልነበረም::
ዘወትር የሚያስበው ስለ ቤተክርስቲያን ዕድገትና ስለ ሀገር ደኅንነት
ነው::

አንድ ጊዜ አስታውሳለሁ አሥመራ እያለን እርሱ የምክር ቤት ምክ
ትል ፕሬዝዳንት በነበረ ጊዜ እናታችን 'ቤታችን ሳሎናችን ምን እንደ
ሚመስል እዩት፣ የእርስዎ ጓደኞች ሚኒስትሮች ከእርስዎ የተሻለ ኑሮ
ነው የሚኖሩት፣ ለልጆችዎስ እንዴት አንድ ነገር አይሠሩም' ትለዋ
ለች:: እርሱም 'እኔ ግን ቅድሚያ ለቤተ ክርስቲያን (ለሃይማኖቴ) እና
ለሀገሬ እንጂ ለራሴ ኑሮና ብልጽግና ብቻ የምሮጥ አይደለሁም::
ልጆቼንም ቢሆን ትምህርታቸውን አስተምሬ ራሳቸውን እንዲችሉ አደ
ርጋለሁ እንጂ ሌላ የምሰጣቸው ነገር የለም' ብሎ መልሶላታል::
ይህንንም ብዙ ሰው ያውቃል:: አባታችን ምንም ነገር ለራሴ ለልጆቼ
አይልም:: አቅሙ በፈቀደ መጠን ለሀገሬና ለቤተ ክርስቲያኔ ነው የሚ
ለው:: እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ለዚሁ ሲወጣ ሲወርድ ነው የኖረው::

በአስተዳደግ በኩልም ቢሆን በጥሩ ሁኔታ ነው ያሳደገን:: ሁላች
ንንም አስተምሮ ለጥሩ ደረጃ አብቅቶናል:: ሁልጊዜ ማታ ከሥራ ስን
መለስ ሰብስቦ ይመክረናል:: መጽሐፍ ቅዱስ ሁላችንም በተራ እናነባለን
እንወያያለን:: የሃይማኖትና የሀገር ፍቅር በውስጣችን እንዲኖር አድርጎ
ነው ያለፈው:: በዚህም በጣም እናከብረዋለን::

አሥመራ በነበርንበት ጊዜ ትምህርት ቤት ለመሄድ ፈልጌ ሹፌሩ
በመኪና እንዲያደርሰኝ ንገርልኝ አልኩት:: እርሱም 'ግደይ ይህቺ
መኪና ለእኔ ሥራ እንጂ አንቺን ት/ቤት ለማድረስ አይደለም የተሰጠ
ችኝ:: የመንግሥት መኪና ስለሆነ አይቻልም በእግርሽ እየሄድሽ ተማሪ'
ብሎ ከለከለኝ:: እኔም በእግሬ ተመላልሼ ተምሬ ትምህርቴን ጨረስኩ::
ይህንን የጠቀስኩት በትንሹ ምን ያህል አነስተኛ መስላ ለምትታይ ነገር
ሁሉ ያደረግ የነበረው ጥንቃቄ ነው::





ከማስታውሰው ጠባዩ አንዱ ምግብ ለብቻው መብላት አይወድም::
የሚቀምሳትም ትንሽ ብትሆን ጠረጴዛው በሰው እንዲሞላ ይፈልጋል::
አንድ ጊዜ ምሳ ተሰናድቶ እንዲበላ ጠራሁት:: ማዕድ የቀረብነው እርሱ
እንዲሁም እኔና ባለቤቴ ነበርን:: ማዕዱ በየዓይነቱ ሞልቷል:: እርሱ
ግን ጠራኝና 'ምነው ጠረጴዛው ባዶ ሆነ ድኻ ሆነ' አለኝ:: እኔም
ሁሉም በየዓይነቱ ቀርቦ እንዴት እንዲህ አልክ አባባ ስለው 'ልጄ ሰው
የሌለበት ጠረጴዛ ድኻ ነው' አለኝ:: እኔም በጎረቤት ያሉትን ጓደኞቼን
ሁሉ ጠርቼ ማዕዱን አብረን ተካፈልን:: ለሰዎች የተለየ ፍቅርና አክ
ብሮት አለው:: ብቻውን መብላትና ብቻውን ማግኘትን አይደ ሰት
በትም::

እናታችን አንድም ቀን የእርሱን ደመወዝ አታውቅም:: በእርግጥ
በቤታችን ውስጥ ሁሉም ነገር አለ:: የምትቸገረው ነገር የለም:: እርሱ
ደመወዙን በውጭ ነው የሚጨርሰው:: ቤተ ክርስቲያን ያሠራል፣ ድኻ
ይረዳል፣ የልማት ተቋማት ያቋቁማል:: ለቤተ ክርስቲያንም ለሀገርም
ጠቃሚ ሥራዎችን ያከናውናል::

በየቀኑ ለድኾች ሳይመጸውት የሚውልበት ቀን አልነበረም:: የለበ
ሰውን ጋቢ /ኩታ/ አውልቆ የሰጠበት አጋጣሚ አለ:: አባታችን በጠባ
ዩም የተለየ ሰው ነበር:: መጠጥ አይጠጣም:: ሁልጊዜ በለውጥ ያም
ናል:: ካላመነበት በስተቀር በይሉኝታ የሚያልፈው አንዳችም ነገር የለ
ውም:: ቤተ ክርስቲያን አሳንፆ በምረቃው ሥነ ሥርዓት ግቢው በምእ
መናን ተሞልቶ ዝማሬው በዐውደ ምሕረት ሲቀርብ መመልከት እጅግ
ያስደስተዋል:: በኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት መጽሐፍ ታትሞ ሲወጣና
ሥርጭት ላይ ሲውል የሚታይበት ስሜት ዛሬም ድረስ አይረሳኝም::
ይህንን የምለው አባቴ ስለሆነ ሳይሆን የሚያውቁት ሁሉ የሚመሰክሩት
እውነት ስለሆነ ነው::

ሌላው ስለ አባታችን የማስታውሰው ከ፲፱፻፶፰ ዓ.ም. ጀምሮ እስከ
ዕለተ ሞቱ ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም እየሄደ ይሳለም ነበር:: መጽ
ሐፍ ማንበብ በጣም ይወዳል:: በተለይ ትንቢተ ነቢያትንና የቅዱስ
ጳውሎስን መልእክታት አዘውትሮ ያነባል:: ሲያነብ እያለቀሰ በኀዘን
ስሜት ነበር ::

አባታችን ወንድሜ ጌዴዎን (የመጀመሪያ ልጁ ነው) ከሞተ በኋላ ብዙም ደስተኛ አልነበረም:: አንድ ቀን መኝታ ቤቱ ሻይ ይገርለት ስሄድ 'ሻዩን መልሺው አልጠጣም ጌዴዎን ልጄ ሞቷል' አለኝ:: በዚህ ጊዜ የጌታችን ሥነ ሥዕል ሥር ቆሞ እንደ ሰው ይነጋገር ነበር:: በጣም ይወደዋል:: እንደ ጓደኛ ነበር የሚተያዩት:: እርሱ ከሞተ በኋላ በቃ መንፈሱ ሁሉ ተሰበረ:: ብዙም አልቆየ እርሱም ልጁን ተከትሎ ዐረፈ::

በሕይወተ ሥጋ እያለ «ልጆቼ እኔንም ሆነ እናታችሁን እግዚአብሔር በሞት በጠራን ጊዜ ነፍስ ከሥጋ ስትለይና በርደተ መቃብር ወቅት ልጆች ስለ መሆናችሁ እንዳታለቅሱ አልከለክልም:: በተረፈ ግን ቀብር ብላችሁ ወደ ወዳጅ ቤተ ዘመድ ፍጹም እንዳትልኩ:: ከመጠን በላይም እንዳታለቅሱ እማፀናችኋለሁ» የሚል ትእዛዝ ሰጥቶናል:: እኛም ለእርሱ ማድረግ የሚገባን ማልቀስና ማዘን ባለመሆኑ ወደፊት ውጭ ያሉት ወንድሞቼ ሲሰባሰቡ ለመታሰቢያነት በእርሱ ስም ሙዚየም ለማሠራት ዕቅድ አለን::» በማለት ወ/ሮ ግደይ ድሜጥሮስ ይገልጻሉ::

ስለ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሀገር ወዳድና የሃይማኖት አባት ስለ ክቡር ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም ማንነት የሀገራችን ታዋቂ ሰዎች እንደሚከተለው ያስቀምጣሉ::

"ንቡረ እድ በሀገራቸው አንድነትና ሃይማኖት ላይ ቀጥተኛ አቋም የነበራቸው፤ በቀላሉ ሊተኩ የማይችሉ ኢትዮጵያዊ ናቸው::»

*አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ*
*የታሪክ ጸሐፊና ተመራማሪ*
*መስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም*

*"ንቡረ እድ ድሜጥሮስ የአገር አንድነትና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ትጉኅ ሐዋርያ ነበሩ::"*

*ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ*
*የትግራይ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩ*

*ምንጭ:- ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (ዶ/ር)*
*- አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት*
*- ትንሣኤ መጽሔት ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ቁጥር ፩፻፴፫*
*- ዜና ሐዋርያት የካቲት ፲፱፻፺፱ ቁ.፳፫ ትግርኛ እትም*
*- ፎኖተ ብርሃን ኅዳር ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ቁ.፫፻፵፩ ትግርኛ እትም*
*- አዲስ ዘመን መስከረም ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም*